# ስለ ኢየሱስ
# የሚጠየቁ ጥያቄዎችና
# መልሶቻቸው

በጆን ፓይፐር ተጻፈ

አዲስ አበባ

2002 ዓ/ም

# ማውጫ

መግቢያ ........ 5

ኢየሱስ ለምንድነው መሞት የነበረበት? ........ **8**

እግዚአብሔር እንዴት ሊወደኝ ይችላል? ........ 12

እግዚአብሔርን ባልወደውስ? ........ 16

ይህን ሁሉ ክፉ ነገር እንዲኖር የሚፈቅደውን እግዚአብሔር

እንዴት ልወደው እችላለሁ? ........ 20

ለምንድነው ሁሉ ነገር ከእግዚአብሔር የተነሣ የሚሆነው? ........ 25

ይህ ሁሉ ምን ይጠቅመኛል? ........ 29

ምን ማድረግ አለብኝ? ........ 35

# ስለ ኢየሱስ

# የሚጠየቁ ጥያቄዎችና

# መልሶቻቸው

በጆን ፓይፐር ተጻፈ

አዲስ አበባ

2002 ዓ/ም

# መግቢያ

**ከሁለት** ሺህ ዓመታት በፊት ደቀመዛሙርቱ በጊዜው በህዝቡ ዘንድ ይወራ ስለነበረው ነገር አንስተው ሲነጋገሩ ኢየሱስ እንዲህ ብሎ ጠየቃቸው፡- «ለመሆኑ ሰዎች የሰውን ልጅ ማን ነው ይላሉ?»፡፡ ስለእርሱ ማንነት የተባለውን ነገር ሁሉ ዘርዝረው ነገሩት፡፡ ሰዎች ስለሚሉት መጠየቁን ትቶ ትኩር ብሎ እያያቸው፣«እናንተስ ማን ትሉታላችሁ?»፡፡

ሌሎች ሰዎች ስለእርሱ የሚያወሩትን መግለጥ ለደቀመዛሙርቱ በጣም ቀላል ነበር፡፡ እኛም ብንሆን ከኢየሱስ ጥያቄ ጋር የምንፋጠጥበት ጊዜ ይኖራል፡፡ ማነው እንላለን?

በተደጋጋሚ የምንሰማው በጣም የተለመደ መልስ አለ፡፡ ይህም ኢየሱስ ታላቅ የግብረ ገብ መመህር ፣ የሚል ነው፡፡ ለአብነት የሚበቃ ፣ እንዲሁም ጠቢብና ርህሩህ ነበረ» የሚል ነው፡፡

«*አንበሳው ጠንቋይዋና ቁምሳጥን*» የተሰኘ መጽሐፍ የደረሰ ሲ ኤስ ሊዊስ የተባለ እንግሊዛዊ ጸሐፊ እንዲህ በማለት እህን የማሳነስ አስተሳሰብ ማስወገድ እንዳለብን ይናገራል፡፡

> እዚህ ላይ ለመከላከል በመሞከር ላይ ያለሁት፣ ብዙ ጊዜ ሰዎች ስለኢየሱስ የሚሉትን ሞኝነት የተሞላበት ነገር የሚናገርን ሰው ነው፡፡ ይህም የሞኝነት

ነገር «ኢየሱስን እግዚአብሔር ነኝ በሚለው አገላለፁ ሳይሆን፣ እንደታላቅ የሞራል መምህር ልቀበለው ዝንጁ ነኝ» ይላል፡፡ ልንለው የማይገባ አንድ ነገር ይህ ነው፡፡ በሥጋ ያለ ሰው ኢየሱስ ያስተማራቸውን ትምህርቶች ቢያስተምር እና የተናገረውን ቢናገር፣ ታላቅ የግብረገብ አስተማሪ ነው አይባልም ነበር፡፡ እንዲህ ያለ ሰው እብድ (እኔ የተቀቀለ እንቁላል ነኝ ብሎ እንደሚያምን ሰው ያለ እብድ) ወይም ደግሞ ከገሃነም የመጣ ሰይጣን ነው ይባል ነበር፡፡ የራሳችሁን ምርጫ ልታደርጉ ይገባል፡፡ ይህ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ነበር፣ ነውም፤ ያለዚያ እብድ ወይም ሰይጣን ነው፡፡ ዝም በል አንተ ሞኝ ልትሉት፣ ልትተፉበት ወይም እንደ ሰይጣን ልትገድሉት ትችላላችሁ፣ ወይም እግሩ ሥር ወድቃችሁ ጌታ እና እግዚአብሔር ብላችሁ ልትጠሩት ትችላላችሁ፡፡ ነገር ግን ታላቅ የግብረገብ አስተማሪ ነው የምንለውን ትርጉም የለሽ ነገር መተው ዓይነት ምርጫም አልተወልንም፡፡

ይህ ኢየሱስን ማን ነው የምትሉት? የሚለው ጥያቄ ልትጠይቁትና እንዲሁም ልትመልሱት የሚገባ በጣም አስፈላጊ ጥያቄ ነው፡፡ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ጆን ፓይፐር የተባለ ጸሐፊ ስለ ኢየሱስ የሚጠየቁትን በጣም የተለመዱ ጥያቄዎች ማለት፤ ማን ነው ? ለምን መጣ? የሠራው ሥራ ምንድነው? እና ስለዚህ ጉዳይ ለምን ግድ ሊለን ይገባል? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራሉ፡፡

ከነዚህ ጥያቄዎች አንዳንዶቹን ጥይቃችሁ ከሆነና፣ በራሳችሁ አሳብና ንድፈ

አሳብ ሳይሆን፣ በእግዚአብሔር ቃል ላይ የተመሠረቱ አንዳንድ መልሶች በመፈለግ ላይ ከሆናችሁ፣ ከእኛ ጋር እንድትገናኙ እንጋብዛችኋለን፤ ለራሳችሁ ደስታ፡፡

## ኢየሱስ ለምንድነ ውሟት የነበረበት?

*«በደሙም በሆነው እምነት፣ እግዚአብሔር*

*የማስተሰረያ መሥዋዕት አድርጎ አቅርቦታል፤ ይህንም ያደረገው ቀድሞ የተፈጸመውን*

*ኃጢአት ሳይቀጣ በትእግሥት በማለፍ ጽድቁን ለማሳየት ነው »* ሮሜ 3፡25

*«ፍቅር ይህ ነው፤ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው ሳይሆን፣ እርሱ*

*እንደወደደንና ስለኃጢአታችን ማስተሰረያ ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው»* 1ዮሐንስ 4፡10

*«ክርስቶስ ስለ እኛ ርግማን ሆኖ ከሕግ ርግማን ዋጅቶናል»* ገላቲያ 3፡13

እግዚአብሔር ፍትሐዊ (ጻድቅ) ባይሆን ኖሮ የገዛ ልጁን ለሥቃይና ለሞት አሳልፎ አይሰጥም ነበር፡፡ እግዚአብሔር ፍቅር ባይሆን ኖሮ አንድያ ልጁን በፈቃደኝነት አሳልፎ አይሰጥም ነበር፡፡ እርሱ ፍትሐዊ (ጻድቅ)፣ አፍቃሪ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ፍቅሩ የርሱን

ፍትሐዊ ነት ለማሟላት ፈቃደኛ ነው፡፡

የእግዚአብሔር ሕግ፡- «አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ» ይላል፤፡፡ ዘዳግም 6፡5፡፡ ነገር ግን ሁላችንም ሌሎች ነገሮችን ከእርሱ አስበልጠን ወድደናል፡፡ ኃጢአት ማለት ይህ ነው ፤ ሌሎች ነገሮችን ከእግዚአብሔር አስበልጠን በመምረጥ እርሱን ሳናከብረው ስንቀርና የመረጥናቸውን ነገሮች ስናደርግ፡፡ ሮሜ 3፡23፣ «ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋል የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል» ይላል፡፡ የምናከብረው በጣም የሚያስደስተንን ነገር ብቻ ነው፤ ያም እግዚአብሔር አይደለም፡፡

ስለዚህ ኃጢአት በጣም ትልቅና በክቡር እግዚአብሔር ላይ የሚፈጸም በደል ስለሆነ ነው ትንሽ አይደለም፡፡ የስድብ ከባድነት የሚያርፈው፣ በተሰዳቢው ክብር ላይ ነው፡፡ የዓለማችን ፈጣሪ እግዚአብሔር የእኛ ፍፁም አክብሮት፣ አድናቆትና ታማኝነት ይገባዋል፡፡ ስለዚህ እርሱን አለመውደድ ስሕተት ሳይሆን፣ ክህደት ነው፡፡ የእግዚአብሔርን ክብር ዝቅ ያደርጋል፣ የሰውን ደስታም ያጠፋል፡፡

እግዚአብሔር ፍትሐዊ እንደ መሆኑ መጠን የምንሠራቸውን ኃጢአቶች ዝም ብሎ ማየት አይሆንለትም፡፡ ቅዱስ ቁጣ ስለሚቆጣ ቅጣት ይገባቸዋል፡፡ ይህንንም ሮሜ 6፡23 ውስጥ ግልጽ አድርጓል «የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና፡፡» ሕዝቅኤል18፡4 ውስጥ ደግሞ፣ «ኃጢአት የምትሠራ ነፍስ እርሷ ትሞታለች» ይላል፡፡ በኃጢአት ላይ የሚያንጃብብ ቅዱስ እርግማን አለ፡፡ ኃጢአትን አለመቅጣት፣ ፍትሃዊ አለመሆን ነው፡፡ እግዚአብሔርን አለማክበርም ትክክል ሁኖ ሊታይ ነው፡፡ ውሸት በእውነት ላይ

ይነግሣል፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡- «በሕግ መጻሕፍት የተጻፈውን ሁሉ የማያደርግ የተረገመ ነው» (ገላትያ 3፡10፤ ዘዳ. 27፡26) የእግዚአብሔር ፍቅር ግን በኃጢአተኛ ሰብዓዊ ፍጡራን ሁሉ ላይ ከሚያንዣብበው እርግማን ጋር አይሆንም፡፡ በመሆኑም ቁጣውን ይሸከምና በርሱ የሚያምኑትን ሰዎች ሁሉ እርግማን ይሸከም ዘንድ እግዚአብሔር የራሱን ልጅ ላከ፤ «ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጅቶናል» (ገላትያ 3፡13)፡፡

ሥርየት የሚለው ቃል ትርጉም ይህ ነው፡፡ የሚገልጠው ምትክ በማቅረብ የእግዚአብሔርን ቁጣ ስለማስወገድ ነው፡፡ ምትክ የተሰጠው በእግዚአብሔር በራሱ ነው፡፡ ምትክ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔርን ቁጣ ማስቀረት ብቻ ሳይሆን፣ ወደራሱ አዛወረው፡፡ ነገር ግን በረደ እንጂ አልተሠረዘም፡፡ በእግዚአብሔር አንቀልድ ወይም ፍቅሩን አናቃል፡፡ የኃጢአታችንን ከባድነትና በእኛ ላይ ያለውን ቁጣ ተገቢነት ካልተገነዘብን፤ በእግዚአብሔር በመወደዳችን እየተደነቅን ፊቱ ለመቆም አንችልም፡፡ ለዚህ ዕድል የማንበቃ መሆናችንን በፀጋ ዓማካይነት ስንረዳ ግን፣ ወደ ክርስቶስ ስቃይና ሞት ተመልክተን እንዲህ እንላለን፡- «ፍቅር ይህ ነው፣ እኛ እግዚአብሔርን እንደወደድነው ሳይሆን፣ እርሱ እንደወደደንና ስለኃጢአታችን ማስተሰሪያም ይሆን ዘንድ ልጁን መላኩ ነው» (1ዮሐ. 4፡10)

## እግዚአብሔር እንዴት ሊወደኝ ይችላል?

*በእርሱ እንደ እግዚአብሔር ጸጋ ባለጠግነት መጠን በደሙ በተደረገ ቤዛነት የኃጢአትን*

*ይቅርታ አገኘን፡፡*

ኤፌሶን 1፡7

*በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ*

*እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስከመስጠት*

*ድረስ ዓለምን እንዲሁ ወዶአልና፡፡*

ዮሐንስ 3፡16

*ለጻድቅ የሚሞት ሰው ማግኘት እጅጉን ያዳግታል፤ ለደግ ሰው ሲል ሊሞት የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርስቶስ ስለእኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን የራሱን ፍቅር ያሳያል፡፡*

ሮሜ 5፡7-8

እግዚአብሔር ለእኛ ያለው ፍቅር ልክ፣ በሁለት ነገሮች ታይቷል፡፡ አንደኛው ፡- ከሠራነው ኃጢአት ቅጣት እኛን በማዳን ሥራው የከፈለው መሥዋዕት መጠን ነው፡፡ ሌላው፣ በሚያድነን ጊዜ የነበረን ለድነቱ ተገቢ ያለመሆናችን መጠን ነው፡፡

የመስዋዕቱን ልክ ወይም ጠመን፣«አንድያ ልጁን እስከመስጠት ድረስ» (ዮሐንስ 3፡16) በሚሉት ቃላት ውስጥ ልንሰማ እንችላለን፡፡ «ክርስቶስ» በሚለው ቃል ውስጥም እንሰማዋለን፡፡ ይህ ክርስቶስ፣ ወይም «የተቀባ» ወይም «መሲህ» በሚለው ግሪከኛ ቃል ላይ የተመሠረተ ስም ነው፤ የታላቅ ክብር መገለጫ ቃል ፡፡ መሲሁ የእስራኤል ንጉሥ የሚሆን ነበር፡፡ ሮማውያንን ድል አድርጎ ለእስራኤል ሰላምና ጸጥታን ያመጣ ነበር፡፡ ሲጠቃለል እንግዲህ፣ ኃጢአተኞችን ያድን ዘንድ እግዚአብሔር የላከው ሰው፣ የእርሱ ልጅ ነበር፤ አንድያ ልጁና የተቀባ የእሥራኤል ንጉሥ፣ እርግጠኛው የዓለም ንጉሥ (ኢሳይያስ 9፡6-7)፡፡

ክርስቶስ ያለፈበትን አሰቃቂ ሞት በዚህ ግንዛቤ ላይ ስንጨምርበት፣ በአብና በወልድ የተከፈለው መስዋዕት፣ ለመግለጥ በማይቻል ሁኔታ ታላቅ፣ በመለኮትና በሰው መካከል ያለውን እርቀት ስንመለከት ደግሞ ፍፁም ነው፡፡ እግዚአብሔር እኛን ለማዳን ይህን መስዋእት መረጠ፡፡

ይህ የማይገባን መሆናችንን በተረዳን መጠን፣ ለኛ ያለው ፍቅር መጠን ይጨምራል፡፡ «ለጻድቅ የሚሞት ሰው ማግኘት እጅጉን ያዳግታል፤ ለደግ ሰው ሲል ሊሞት የሚደፍር ምናልባት ይገኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ገና ኃጢአተኞች ሳለን ክርሰቶስ ስለእኛ ሞተ፤ ይህም እግዚአብሔር ለእኛ ያለውን ፍቅር ያሳያል» (ሮሜ 5፡7-8) ፡፡ የሚገባን መለኮታዊ መስዋእት ሳይሆን፣ መለኮታዊ ቅጣት ነበር፡፡ እንዲህ ሲባል ሰምቻለሁ፡- «እግዚአብሔር ለእንቁራርቶች አልሞተም፤ እንደሰብዓውያን ለእኛ ፋይዳ ነበር አፀፋ የሚሰጠው »፡፡ ይህ አባባል ፀጋን በራሱ ነው የሚያቆመው፡፡ እኛ

ከእንቁራርቶች እጅግ የላቅን ነን። እንቁራርቶች ኃጢአት አልሠሩም። አላመኑም፤ እግዚአብሔርንም አስቆጥተው በሕይወታችን ላይ ፋይዳ ያለውን ነገር እንዳያከናውን አላደረጉም። እግዚአብሔር ለእንቁራርቶች መሞት አልተገባውም። አስከፊዎች አልነበሩም። እኛ ግን ነን። የነበረብን እዳ መለኮታዊ መስዋዕት ብቻ ሊከፍለው የሚችልና ታላቅ ነው።

እግዚአብሔር ለእኛ የፈፀመውን መስዋዕት የሚገልጥ አንድ ማስገንዘቢያ ብቻ ነው ያለው። እኛ አይደለንም። «እንደእግዚአብሔር ባለጠግነት መጠን» (ኤፌሶን 1፡7) ነው። ሙሉ በሙሉ ነፃ ነው። የተገባን ነገር ስለሆነ የተሰጠ አፀፋ አይደለም። ፍፁም የሆነው የ ሙሉነት ነው። የመለኮታዊው ፍቅር መጨረሻም ይህ ነው፤ ለኃጢአተኞች ግንዛቤ የሚመስጥ ፍቅር፣ ታላቅ ዋጋ የተከፈለበት። ፍፁም የሆነ ውብቱ ከሁሉ በላቀ ሁኔታ ለዘላለም ደስተኞች የሚያደርገን ።

# እግዚአብሔርን ባልወደውስ?

*በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤*

*በወልድ የማያምን ግን የእግዚአብሔር ቁጣ*

*በላዩ ይሆናል እንጂ ሕይወትን ኣያይም፡፡*

ዮሐንስ 3፡36

*እነዚህም ወደዘላላም ፍርድ ፣ ጻድቃን ግን*

*ወደዘላላም ሕይወት ይሄዳሉ፡፡*

ማቴዎስ 25፡46

*እነርሱም ከጌታ ፊትና ከኃይሉ ክብር ተወግደው*

*በዘላላም ጥፋት ይቀጣሉ፡፡*

2ተሰሎንቄ 1፡9

ደስተኞች  በምንሆንባቸው ጊዜያት ለመሞት አንፈልግም፡፡  መከራችን የከበደ ሲመስለን ብቻ ነው የመሞት ምኞታችን ከፍ የሚለው፡፡ በነዚያ ጊዜያት በእርግጥ የምንፈልገው፣

ሞትን ሳይሆን ፋታ ነው፡፡ መልካሙ ጊዜ እንደገና ቢመጣ እንወዳለን፡፡ ስቃዩ እንዲሄድልን እንፈልጋለን፡፡ የምንወደው ሰው ከመቃብር ተነስቶ ቢመጣልን እንፈልጋለን፡፡ ሕይወትና ደስታን እንሻለን፡፡

ሞትን የጥሩ ሰው ሕይወት ፍፃሜ አድርገን ስናቀርብ እራሣችንን ነው የምናታልል፡፡ ሞት ጠላት ነው፡፡ ከዚህ ዓለም አስደናቂ ደስታዎች ሁሉ ይለየናል፡፡ ሞትን በጥሩ ስም የምንጠራው ከክፉ ነገሮች ሁሉ አናሳ እንደሆነ አድርገን ነው፡፡ በስቃያችሁ ላይ የሚፈፀመው የሞት ፍርድ የመከራችሁ ሳይሆን፣ የተስፋችሁ ፍፃሜ ነው፡፡ የሰዎች ልብ ናፍቆት፣ መኖርና ደስተኛ መሆን ነው፡፡

እግዚአብሔር የፈጠረን፣ «በሰዎች ልብ ዘላለማዊነትን አኖረ» (መክብብ 3፡11) በሚለው ሁኔታ ነው፡፡ የተፈጠርነው በእግዚአብሔር አምሳል ነው፤ እርሱ ሕይወትን ስለሚወድ ለዘላለም ይኖራል፡፡ ለዘላለም እንድንኖር ነው የተፈጠርነው፡፡ እንኖራለን፡፡ የዘላለም ሕይወት ተቃራኒ አለመኖር ነው፤ ሲኦል፡፡ ኢየሱስ ስለሞት ከማንም ይልቅ በመናገር፣ እርሱ የሚሰጠውን የዘላለም ሕይወት አለመቀበል ውጤቶቹ መጥፋት ሳይሆን፣ የእግዚአብሔር አስከፊ ቁጣ መሆኑን በግልፅ ተናግሯል፡፡ «በወልድ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት አለው፤ በወልድ የማያምን ግን፣ የእግዚአብሔር ቁጣ በላዩ ይሆናል እንጂ ሕይወትን አያይም» (ዮሐንስ 3፡36)፡፡

ይህ ለዘላለም የሚኖር ነው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ «እነዚህም ወደ ዘላለም ፍርድ፣ ጻድቃን ግን ወደዘላለም ሕይወት ይሄዳሉ» (ማቴዎስ 25፡46)፡፡ ይህ የሚያመለክተው፣ እግዚአብሔርን ችላ ማለት ወይም መናቅ ሊነገር የማይቻል ፍፁም ክፉ

ነገር የመሆኑን እውነት ነው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ «ዓይንህ ብታሰናከልህ ጐልጉለህ አውጣት፤ ሁለት ዓይን ኖሮህ ወደ ገሃነም ከመጣል፣ አንድ ዓይን ኖሮህ ወደእግዚአብሔር መንግሥት መግባት ይሻላል፤ በገሃነም ትሉ አይሞትም፤ እሳቱ ይጠፋምና» (ማርቆስ 9፡47-48)

ስለዚህ፣ ዘላለማዊ ሕይወት፣ በቀላሉ ከችግርና ከደስታ ጋር ቀጣይ አይደለም፡፡ አሁን ያለው ሕይወት አስከፊ ፍፃሜ፣ ገሀነም ከመሆኑ ጋር ሲነፃፀር፣ ዘላለማዊ ሕይወት ከሁሉ የተሻለ ነው፤ ኃጢአትና ሀዘን ሁሉ የማይኖሩበት፣ ከሁሉ የላቀና ሁሌ የሚጨምር ደስታ ያለበት፡፡ በዚህ በወደቀ ተፈጥሮ ውስጥ ያሉ ክፉና ጎጂ ነገሮች ሁሉ ይወገዳሉ፡፡ ጥሩ ነገር ሁሉ- እውነተኛና ዘላለማዊ ደስታ የሚያመጣ ነገር ሁሉ- ይጠበቃል፣ ይጠራል፣ ይስፋፋል፡፡

በዚህ ዓለም ሊታሰብ ለማይቻለው ሁለገብ ደስታ እንድንበቃ እንለወጣለን፣ «ዓይን ያላየውን ጆሮ ያልሰማውን የሰውም ልብ ያላሰበውን እግዚአብሔር ለሚወዱት አዘጋጅቷል» (1ቆሮንቶስ 2፡9)፡፡ በክርስቶስ ለሚያምኑ፣ በማንኛውም ጊዜ፣ አሁንና ሁልጊዜ፣ ከሁሉ የላቀ ነገር ገና ይመጣላቸዋል፡፡ ለሁሉ የሚበቃውን የእግዚአብሔርን ክብር እናያለን፣ «እውነተኛ አምላክ የሆነከውን አንተንና የላከኸውንም ኢየሱስ ክርሰቶስን ያውቁ ዘንድ ይህች የዘላለም ሕይወት ናት» (ዮሐንስ 17፡3)፡፡ ለዚህ ነው ክርስቶስ የተሰቃየውና የሞተው፡፡ ታዲያ እንዴት ነው እሱን እንደትልቅ ሀብትና ሕይወት አቅፈን የማንይዘው ?

## ይህ ሁሉ ክፉ ነገር እንዲኖር የሚፈቅደውን እግዚአብሔር እንዴት ልወደው እችላለሁ?

*እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፣ እግዚአብሔር ግን ዛሬ*

*እንደሚታየው ሁሉ የብዙዎችን*

*ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው፡፡*

ዘፍጥረት 50፡20

*በእርግጥ ሄሮድስና ጴንጤናዊው ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል*

*ሕዝብ ጋር በዚህች ከተማ አንተ በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ*

*በኢየሱስ ላይ ለማሤር ተሰበሰቡ፤ ይህም የሆነው  የአንተ*

*ክንድና ፈቃድ ጥንት የወሰኑት እንዲፈፀም ነው፡፡*

ሐዋርያት *ሥራ* 4፡27-28፡፡

*«ምስጢር የሆነው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው»*

ዘዳግም 29፡29፡፡

ስለክፉ እንዲሁም ስለስቃይ ልናገር የምችለው ተመራጭና ትልቅ ነገር፣ እግዚአብሔር በኢየሱስ በከል ገብቶ ወደመልካምነት የለወጠው መሆኑን ነው፡፡ የክፉ መነሻ

ምስጢርነቱ እንዳለ ነው፡፡ ምስጢር የሆነው ነገር መጠሪያ «ነፃ ምርጫ » የሚል ይሆናል፡፡ ፍፁም የሆነው አንድ ፍጡር ኃጢአት መፈፀምን የመረጠበትን ምክንያት አይገልጥም፡፡ የምስጢሩ ሌላ ስም «የእግዚአብሔር ልዕልና» የሚለው ነው፡፡ እውነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመሆኑን ያህል፣ ይህ ምስጢርም ጥያቄዎችን ያለመልስ ይተዋቸዋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለመሄድ የምንፈልገውን እርቀት አያስኬሄደንም፡፡ ይልቁንም እንዲህ ነው የሚለን፣ «ምስጢር የሆነው ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው»(ዘዳግም 29፡29)

የመጽሐፍ ቅዱስ ልብና የክርስትና ልብ፣ ከፉ ከየት እንደመጣ አይገልጥም፡፡ እግዚአብሔር እንዴት በዚያ ገብቶ ፍፁም ተቃራኒ ወደሆነ ዘላለማዊ ጽድቅና ደስታ እንደሚለውጠው ነው የሚያመለክተው፡፡ ለመሲሁ እንዲህ እንደሚሆን የሚጠቁሙ ነገሮች በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነበሩ፡፡ የያዕቆብ ልጅ ዮሴፍ ወደግብፅ በባርነት ተሸጠ፡፡ በአሥራ ሰባት ዓመት የተተወ መሰለ፡፡ እግዚአብሔር በሁነቱ ውስጥ ስለነበረ ግን፣ የሸጡትን ሰዎች፤ በታላቅ ርሀብ ጊዜ እንዲያድናቸው ግብፅ ውስጥ መሪ አደረገው፡፡ ታሪኩ የሴፍ ለወንድሞቹ እንዲህ በማለት በተናገረው ቃል ውስጥ ተጠቃሏል፦ «እናንተ እኔን ለመጉዳት አስባችሁ አድርጋችሁት ነበር፤ እግዚብሔር ግን ዛሬ እንደሚታየው ሁሉ የበዙዎችን ሕይወት ለማዳን ለበጎ ነገር አዋለው»(ዘፍጥረት 50፡20)

ስለኢየሱስ የተነገረ ትንቢት፤ ያድን ዘንድ የተተወ ወይም የኢየሱስን ቅድመ አያቶች አስቡ፡፡ በአንድ ወቅት እግዚብሔር ብቸኛው የእሥራኤል ንጉሥ ነበር፡፡ ሕዝቡ ግን አመፁና ሰብዓዊ ንጉሥ ጠየቁ፣ «አይሆንም፣ ንጉሥ እንዲነግሥልን እንፈልጋለን»(1ሳሙ. 8፡19) አሉ፡፡ በኋላ ግን እንዲህ በማለት ንስሀ ገቡ፣«ሌላው

በደላችን ሳያንስ፣ ንጉሥ እንዲነግሥልን በመጠየቃችን ተጨማሪ ክፋት አደረግን»(1ሳሙ. 12፡19)፡፡ እግዚአብሔር ግን በዚያውስጥ ነበር፡፡ ከነዚህ ነገሥታት ክርስቶስን ወደዓለም አመጣ፡፡ ኃጢአት የለሹ አዳኝ ኃጢአተኞችን ለማዳን ሲመጣ፣ መነሻው ከኃጢአት ውሰጥ ነበር፡፡

አስደናቂው ነገር ግን፣ ክፉው ነገርና ስቃዩ፣ እራሱን ክፉንና ስቃይን ድል ለማድረጊያነት ለክርስቶስ የተሰጠው መንገድ መሆኑ ነው፡፡
በኢየሱስ ላይ የሚፈፀም ማንኛውም የክህደት እና የጭካኔ ድርጊት ኃጢአትና ክፉ ሥራነበር፡፡ ቢሆንም እግዚአብሔር በውስጡ ነበር፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፣ «እግዚአብሔር በጥንት ውሳኔውና በቀደመው ዕውቀቱ ይህን ሰው አሳልፎ በእጃችሁ ሰጣችሁ፤ እናንተም በክፉ ሰዎች እጅ ሰቀላችሁ ገደላችሁት» (ሐዋርያት ሥራ 2፡23)፡፡ ጀርባው ላይ ያረፈው ግርፋት፣ የራሱ ላይ የሾህ አክሊል፣ ጉንጩ ላይ የተተፋበት ምራቅ፣ የፊቱ ላይ ሰንበር፣ እጁ የተቸነከረባቸው ሚስማሮች፣ ጎኑ የተወጋበት ጦር፣ የገዢዎች ስድብ፣ የወዳጁ ክህደት፣ የደቀመዛሙርቱ ትተውት መሄድ፡፡ እነዚህ ሁሉ የኃጢአት ውጤቶች ሲሆኑ፣ የኃጢአትን ኃይል ለማጥፊያነት በእግዚአብሔር የታቀዱ ነበሩ፡፡ «በእርግጥም ሄሮድስና ጳንጥዮስ ጲላጦስ ከአሕዛብና ከእስራኤል ሕዝብ ጋር በዚህች ከተማ አንተ በቀባኸው በቅዱሱ ብላቴናህ በኢየሱስ ላይ ለማሤር ተሰበሰቡ፡፡ ይህም የሆነው የአንተ ክንድና ፈቃድ ጥንት የወሰኑት እንዲፈፀም ነው» (ሐዋርያት ሥራ 4፡27-28)

የእግዚአብሔርን ልጅ ከመጥላትና ከመግደል የከፋና የገዘፈ ኃጢአት የለም፡፡ ከክርስቶስ ስቃይ የላቀ ወይም ከእርሱ የበለጠ በደል አልባነት (ንፅህና) አልነበረም፡፡
ቢሆንም እግዚአብሔር በዚያ ሁሉ
ውሰጥ ነበር፣ «መድቀቁና መሰቃየቱ ግን የእግዚአብሔር ዓላማ፣ ክፉና ስቃይን ማጥፋት ነበር፣» (ኢሳይያስ 53፡10) ይህ አሠራር ታዲያ፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ስቃይ፣ በእረሱ በኩል ዘላለማዊ ጽድቅና ደስታ እንዳያመጣ የሚያግደው ኃጢአት ወይም ክፉ ነገር

እንደሌለ እግዚአብሔር ለዓለም ያሳየበት አይደለም? በእኛ በኩል የተፈጠረው ያው ስቃይ፣ የድነታችን ተስፋ ሆነ፣ «አባት ሆይ፤ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው » (ሉቃስ 23፡34)

**እግዚአብሔር ሕይወትና ደስታን እንዲሰጠን አንድያ ልጁን ኢየሱስን ላከው፡፡**

*ክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደዓለም መጣ...* 1ጢሞቴዎስ 1፡15

ክርስቶስ እንደእኛ ላሉ ኃጢአተኞች መሞቱ ነው የምሥራቹ ፡፡ የሞቱን የማዳን ኃይል ዋጋ ያለው ለማድረግና የዘላለምን ሕይወት፣ እንዲሁም የደስታን በር ለመክፈት በአካል ከሞት ተነሣ፡፡ (1ቆሮንቶስ 15፡20) የዚህ ትርጉሙ፣ እግዚብሔር በደለኛ ኃጢአተኞችን ነፃ በማድረግም ፃድቅ ይሆናል ማለት ነው (ሮሜ 3፡25-26) «እንዲህም ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለኃጢአት ሞቶአልና፤ ወደእግዚብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ፣ ጻድቅ የሆነው እርሱ፣ ስለአመፀኞች ሞተ» (1ጴጥሮስ 3፡18) ወደ እግዚአብሔር መግባት ጥልቅና ዘላለማዊ እርካታ ባለበት ሥፍራ መሆን ነው፡፡

**በክርስቶስ ደም ዓማካይነት የተገኙ ጥቅሞች፣ ንስሐ የሚገቡና በእርሱ የሚታመኑ ሰዎች የሚያገኙዋቸው ናቸው፡፡**

*በጌታ በኢየሱስ እመን፣ አንተም ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ ፡፡*

*ሐዋርያት ሥራ 16፡31*

«ንስሐ መግባት» ማለት ፣ ውሸት ከሆኑት የኃጢአት ተስፋዎች ሁሉ መላቀቀ ማለት ነው፡፡ «እምነት» ማለት፣ በኢየሱስ በኩል እንዲሆንልን እግዚአብሔር በሰጠን ተስፋዎች ሁሉ መርካት ነው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ « ወደእኔ የሚመጣ ...ፈፅሞ አይጠማም » (ዮሐንስ 6፡35) ድነታችንን እራሳችን አናገኘውም፡፡ በችሎታችን ልናመጣው አንችልም (ሮሜ 4፡4-5) በእምነት ዓማካይነት በጸጋ ስጦታ ነው (ሮሜ 3፡24) ከነገሮች ሁሉ በላይ ዋጋ ከሰጠነው እናገኘዋለን (ማቴዎስ 13፡44) ይህን ስናደርግ እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለው ዓላማ ይፈፀማል—እርሱ በእኛ ይከብራል እኛ በርሱ እንረካለን—ለዘላለም፡፡

## ለምንድነው ሁሉ ነገር ከእግዚአብሐር የተነሣ የሚሆነው?

*እንዲሁም ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለኃጢአት*

*ሞቶአልና፤ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ*

1ጴጥሮስ 3፡18

*አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ*

*ደም አማካይነት ቀርባችኋል፡፡*

ኤፌሶን 2፡13

*እኔም ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ አቀናለሁ፤ ፍፁም ደስታዬ ወደሆነው አምላክ*

*እሄዳለሁ፡፡*

*መዝሙር* 43፡4

ሁሉም ነገር ሲነገርና ሲከናወን፣ ወንጌሉ ወይም መልእክቱ እግዚአብሔር ነው፡፡ ወንጌል ማለት «የምስራች» ነው፡፡ ክርስትና መጀመሪያ ነገረ መለኮት ሳይሆን ዜና ነው፡፡ የጦር ምርኮኞች በተደበቀ ራዲዮ ዓማካይነት የሚያዳምጡት፣ አጋር ጦር በአቅራቢያው መድረሱንና ነፃ የመውጣታቸው ነገር የጊዜ ጉዳይ ብቻ መሆኑን የሚረዱበት ነው፡፡ ጠባቂዎቹ የምርኮኞችን ደስታ አይተው በምክንያቱ ግራ በመጋባት ይገረማሉ፡፡

በምሥራቹ ውስጥ ያለው የመጨረሻ ጥሩ ነገር ምንድነው? በአንድ ነገር ይፈፀማል፣ በእግዚብሔር በራሱ፡፡ የወንጌሉ ቃላት ሁሉ ወደሱ ይመራሉ፤ ይህ ካልሆነ የምሥራች አይደሉም፡፡ ለምሳሌ፣ ድነት ከሲኦል የሚያድን ብቻና ወደ እግዚአብሔር የማያደርስ ከሆነ፣ የምሥራች አይደለም፡፡ «ይቅርታ» ከጥፋተኛነት የሚያሳርፍ ብቻ ከሆነና ወደ እግዚአብሔር መሄጃውን መንገድ የማይከፍት ከሆነ፣ የምሥራች አይደለም፡፡ «ጽድቅ» በእግዚአብሔር ተቀባይነትን ብቻ እንጂ፣ ከእርሱ ጋር አንድነትን የማያመጣ

ከሆነ ፣ የምሥራች አይደለም፡፡ «የእግዚአብሔር ልጅ መሆን» ወደ እርሱ ቤተሰብነት ብቻ እንጂ በእጆቹ ላይ የማያሳርፈን ከሆነ፣ የምሥራች አይደለም፡፡

ይህ ወሳኝ ነገር ነው ፡፡ ብዙ ሰዎች ያለ እግዚአብሔር የምሥራቹን ብቻ ያቀፉ ይመስላሉ፡፡ ከሲኦል ለማምለጥ በመፈለጋችን ብቻ አዲስ ልብ ያለን ለመሆኑ እርግጠኛ ማስረጃ አይሆንም፡፡ ይህ ፍፁም የሆነ ተፈጥሯዊ ፍላጎት እንጂ፣ ልዕለ ተፈጥሮአዊ አይደለም፡፡ የይቅርታን ሥነ ልቦናዊ ፈውስ ለመፈለግ ፣ ወይም የእግዚአብሔርን ቁጣ ለማስወገድ፣ ያለዚያም የእግዚብሔርን ዓለም ለመውረስ አዲስ ግንዛቤ አይፈልግም፡፡ እነዚህ ሁሉ ያምንም መንፈሳዊ ለውጥ የሚታወቁ ናቸው፡፡ እነዚህን ነገሮች ለመሻት ዳግም መወለድ አያሻችሁም፡፡ አጋንንትም ይፈልጓቸዋል፡፡

እነዚህን መፈለግ ስህተተ አይደለም፡፡ አለመፈለጉ ሞኝነት ነው፡፡ የመለወጣችን ማስረጃ፣ እነዚህ ነገሮች ወደ እግዚአብሔር ደስታ የሚያደርሱን ስለሆኑ የምንፈልጋቸው መሆናችን ነው፡፡ ይህ ነው ክርስቶስ የሞተለትን ከሁሉ የላቀ ነገር፡፡ «እንዲሁም ክርስቶስ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለኃጢአት ሞቶአልና፤ ወደእግዚአብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ ጻድቀ የሆነው እርሱ ስለዐመፀኞች ሞተ» (1ጴጥሮስ 3፡18)፡፡

ለምንድነው ይህ የምሥራቹ ፍሬ ነገር የሆነው? ምክንያቱ፣ የእግዚአብሔርን ክብር በማየትና በመደሰት ሙሉና ዘላለማዊ ደስታን
እንድንለማመድ መደረጋችን ነው፡፡ ከሁሉ የላቀው ደስታችን ከዚህ ካነሰ ነገር የሚመጣ ከሆነ ፣ ጣኦት አምላኪዎች ነን፣ እግዚአብሔርንም አላከበርነውም፡፡ የፈጠረን የእርሱ ክብር በዚያ ባለን ደስታ እንዲገለጥ አድርጎ ነው፡፡ የክርስቶስ ወንጌል በልጁ ሕይወት ዋጋነት የገኘ የምሥራች ነው፡፡ እግዚአብሔር አስፈላጊውን ነገር ሁሉ ያደረገው፣

ለዘላለምና ለሁልጊዜ በሚጨምር ደስታ ፣ ማለት በራሱ ሊመስጠን ነው፡፡

ክርስቶስ ከመምጣቱ ረዘም ባለ ጊዜ፣ እግዚአብሔር የሙሉና ዘላለማዊ ደስታ ምንጭ አድርጎ እራሱን ገለጠ፡፡ «የሕይወትን መንገድ ታሳየኛለህ፤ በአንተ ዘንድ የደስታ ሙላት፣ በቀኝህም የዘላለም ፍስሐ አለ » (መዝ. 16፡11) ፡፡ ከዚያ በኋላ ይሰቃይና «ወደእግዚአብሔር ያቀርበን ዘንድ» ክርስቶስን ላከው፡፡ ማለት ክርስቶስን የላከው፣ ሰብዓዊ ፍጡር ሊኖረው ወደሚችለው እጅግ ጥልቅና ረጅም ደስታ እንዲያደርሰን ነው፡፡ ጥሪው ወይም ግብዣው እንዲህ ይላል፣ «በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ» (ዕብራዉያን 11፡25) ተመለሱና «ወደዘላለም ደስታ ኑ»፡፡ ወደ ክርስቶስ ኑ፡፡

## ይህ ሁሉ ምን ይጠቅመኛል?

*በእግዚአብሔር ልጅ ስም የምታምኑ እናንተ የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ታውቁ ዘንድ ይህን እጽፍላችኋለሁ፡፡*

1ዮሐንስ 5፡13

*ቃሌን የሚሰማ፣ በላከኝም የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ ከሞት ወደሕይወት ተሻገረ እንጂ ወደ ፍርድ አይመጣም፡፡*

ዮሐንስ 5፡24

*እንግዲህ ኃጢአታችሁ እንዲደመሰስ ንስሐ ግቡ፤*

*ከመንገዳችሁም ተመለሱ፡፡*

ሐዋርያት ሥራ 3፡19

*ወደዘላለም ሕይወት የሚያደርሳችሁን የጌታችንን*

*የኢየሱስ ክርስቶስን ምሕረት ስትጠብቁ ሳለ በእግዚአብሔር*

*ፍቅር ራሳችሁን ጠብቁ፡፡*

ይሁዳ 1፡21

## እግዚአብሔር ለክብሩ ነው የፈጠረን

*ወንዶች ልጆቼን ከሩቅ፣ ሴቶች ልጆቼንም ከምድር ዳርቻ ... ለክብሬም የፈጠርሁትን ... አምጡ፡፡*
ኢሳይያስ 43፡6-7

እግዚአብሔር የፈጠረን፣ ታላቅነቱን እንድናገን ነው፡፡ መልካምነቱን፣ እውነትና ውበቱን፣ ጥበቡንና ፅድቁን እንድናሳይ ጭምር፡፡ የእግዚብሔርን ክብር የማሳያ ታላቅ ነገር የሚመጣው፣ በእርሱነቱ ሙላት ከሚሰማን ጥልቅ ደስታ ነው፡፡ የዚህ ትርጉሙ፣ እግዚአብሔር ይከብራል፣ እኛ ደግሞ ደስ ይለናል ማለት ነው፡፡ እግዚብሔር የፈጠረን፣ እኛ በእርሱ ስንረካ፣ በዚያ እርሱ እጅግ እንዲከብር ነው፡፡

## ሰብዓዊ ፍጡር ሁሉ ለእግዚብሔር ክብር መኖር አለበት፡፡

*እንግዲህ ስትበሉም ሆነ ስትጠጡ፣ ወይም ማንኛውንም ነገር ስታደርጉ፣ ሁሉንም ነገር ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት፡፡* 1ቆሮንቶስ 10፡31

እግዚአብሔር ለክብሩ ከፈጠረን፣ ለእርሱ ክብር መኖር የሚኖርብን መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ ኃላፊነታችን የሚመጣው ከአቅዱ ነው፡፡ በመሆኑም፣ የመጀመሪያ ግዴታችን፣ እርሱ ለእኛ በሆነልን ሁሉ በመርካት የእርሱን ፋይዳ ማሳየት ነው፡፡ ይህ

ነው እግዚአብሔርን የመውደድ (ማቴዎስ 22፡37) እና በእርሱ የመታመን (ዮሐንስ 5፡3-4) መሠረታዊ ነገር፡፡ የእውነተኛ መታዘዛችን፣ በተለይም ሌሎችን የመውደዳችን (ቆላስያስ 1፡4-5) ሁሉ ሥረ ነገር ይህ ነው፡፡

## ሁላችንም ማድረግ እንደሚገባን እግዚብሔርን አላከበርነውም፡፡

*ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋል፤ የእግዞብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፡፡ ሮሜ 3፡23*

«የእግዚብሔር ክብር ጎድሎአቸዋል» ማለት ምን ማለት ነው? ማንኛችንም እንደሚገባን በእርሱ አልታመንም፣ አላከበርነውም ማለተ ነው፡፡ በታላቅነቱ ረክተን በእርሱ መንገድ አልሄድንም፡፡ እርካታን ከሌሎች ነገሮች በመፈለግ ከእግዚአብሔር የበለጡ ፋይዳዎችን አደረግናቸው፡፡ ይህ ሁኔታ በመሠረቱ ጣኦት አምልኮ ነው (ሮሜ 1፡21-23) ኃጢአት ወደዓለም ከመጣበት ጊዜ ጀምሮ፣ እግዚአብሔርን እንደከበረ እርካታችን አርገን መቀበልን በጣም እምቢ በማለት ላይ ነን (ኤፌሶን 2፡3) ይህ በእግዚአብሔር ታላቅነት ላይ የሚደረግ አሰቃቂ በደል ነው (ኤርምያስ 2፡12-13)

## ሁላችንም ከእግዚብሔር ተገቢ ፍርድ በታች ነን፡፡

የኃጢአት ደሞዝ ሞት ነውና

ሮሜ 6፡23

ሁላችንም የእግዚብሔርን ክብር አንኳሰናል፡፡ እንዴት? ከእርሱ በላይ ሌሎች ነገሮችን በመምረጥ፡፡ ባለማመስገን፣ በእርሱ ባለመታመንና ባለመታዘዝ፡፡

በመሆኑም እግዚአብሔር ለዘላለም በክብሩ ደስተኞች እንዳንሆን በመከልከሉ ትክክል ነው፤ «እነርሱም ከጌታ ፊትና ከኃይሉ ክብር ተወግደው በዘላለም ጥፋት ይቀጣሉ» (2ተሰሎንቄ 1፡9

«ገሀነም ወይም ስኦል» የሚለው ቃል አዲስ ኪዳን ውስጥ አሥራ ሁለት ጊዜ ተጠቅሷል፡፡ አሥራ አንድ ጊዜ በኢየሱስ በራሱ፡፡ ይህ በተከፉ ወይም በተቆጡ ሰባኪዎች የተፈጠረ አፈታሪክ አይደለም፡፡ ኃጢአተኞችን ከፍርዱ ነፃ ለማውጣት ከሞተው የእግዚብሔር ልጅ የተላለፈ ከባድ ማስጠንቀቂያ ነው፡፡ ችላ ብንለው ከባድ አደጋ ነው የሚጠብቀን፡፡

መጽሐፍ ቅዱስ ስለሰብዓዊ ፍጡር ሁኔታ የሚያደርገውን ትንታኔ እዚህ ላይ ቢያቆም ኑሮ፣ ተስፋ በሌለው የወደፊት ጭለማ ውስጥ እንወድቅ ነበር፡፡ ደግነቱ፣ ነገሩ እዚህ ላይ አይደለም የሚቆመው፡፡

**እግዚአበሔር ሕይወትና ደስታን እንዲሰጠን አንድያ ልጁን ኢየሱስን ላከው፡፡**

*ክርስቶስ ኢየሱስ ኃጢአተኞችን ለማዳን ወደዓለም መጣ...* 1ጢሞቴዎስ 1፡15

ክርስቶስ እንደእኛ ላሉ ኃጢአተኞች መሞቱ ነው የምሥራቹ ፡፡ የሞቱን የማዳን ኃይል ዋጋ ያለው ለማድረግና የዘላለምን ሕይወት፣ እንዲሁም የደስታን በር ለመክፈት በአካል ከሞት ተነሣ፡፡ (1ቆሮንቶስ 15፡20) የዚህ ትርጉሙ፣ እግዚብሔር በደለኛ ኃጢአተኞችን ነፃ በማድረግም ፃድቅ ይሆናል ማለት ነው (ሮሜ 3፡25-26) «እንዲህም ክርስቶስ

ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ስለኃጢአት ሞቶአልና፤ ወደእግዚብሔር ያቀርባችሁ ዘንድ፣ ጻድቅ የሆነው እርሱ፣ ስለአመፀኞች ሞተ» (1ጴጥሮስ 3፡18) ወደ እግዚአብሔር መግባት ጥልቅና ዘላለማዊ እርካታ ባለበት ሥፍራ መሆን ነው፡፡

## በክርስቶስ ደም ዓማካይነት የተገኙ ጥቅሞች፣ ንስሐ የሚገቡና በእርሱ የሚታመኑ ሰዎች የሚያገኙዋቸው ናቸው፡፡

*በጌታ በኢየሱስ እመን፣ አንተም ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ ፡፡*

*ሐዋርያት ሥራ 16፡31*

«ንስሐ መግባት» ማለት ፣ ውሸት ከሆኑት የኃጢአት ተስፋዎች ሁሉ መላቀቅ ማለት ነው፡፡ «እምነት» ማለት፣ በኢየሱስ በኩል እንዲሆንልን እግዚአብሔር በሰጠን ተስፋዎች ሁሉ መርካት ነው፡፡ ኢየሱስ እንዲህ ብሏል፣ « ወደእኔ የሚመጣ ...ፈፅሞ አይጠማም » (ዮሐንስ 6፡35) ድነታችንን እራሳችን አናገኘውም፡፡ በችሎታችን ልናመጣው አንችልም (ሮሜ 4፡4-5) በእምነት ዓማካይነት በጸጋ ስጦታ ነው (ሮሜ 3፡24) ከነገሮች ሁሉ በላይ ዋጋ ከሰጠነው እናገኘዋለን (ማቴዎስ 13፡44) ይህን ስናደርግ እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለው ዓላማ ይፈፀማል—እርሱ በእኛ ይከብራል እኛ በርሱ እንረካለን—ለዘላለም፡፡

## ምን ማድረግ አለብኝ?

*አንድ ሰው ወደሱ እየሮጠ መጣ፤ በፊቱም በጉልበቱ ተንበርክኮ፣*

*«ቸር መምህር ሆይ፣ የዘላለምን ሕይወት ለመውረስ ምን*

*ማድረግ ይገባኛል» አለው*

ማርቆስ 10፡17

*እየተንቀጠቀጠም በጳውሎስና በሲላስ እግር ላይ ወደቀ፤*

*... እናንተ ሰዎች እድን ዘንድ ምን ላድርግ» አላቸው፡፡*

*እነርሱም «በጌታ በኢየሱስ እመን፤ አንተም ቤተሰቦችህም*

*ትድናላችሁ» አሉት፡፡*

ሐዋርያት *ሥራ* 16፡29-30

- ከኃጢአት ሐሰተኛ ተስፋዎች ተለይ
- ከበደለኛነት፣ ከቅጣትና ባርነት እንዲያድንህ ኢየሱስን ጠይቀው፡- «የጌታን ስም የሚጠራ ሁሉ ይድናል» (ሮሜ 10፡13)

- ተስፋህን ሁሉ፣  እግዚአብሔር በኢየሱሱ በኩል ያንተ በመሆኑ ላይ ማኖርን ጀምር፡፡
- የኃጢአትን ተስፋዎች ኃይል፣ ከሁሉ በላቀው የእግዚብሔር ተስፋዎች እርካታ አፍርሳቸው፡፡
- ነፃ የሚያወጡህን በጣም ክቡርና በጣም ትልቅ ተስፋዎች ለመረዳት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ጀምር፣ (2ጴጥሮስ 1፡3-4)
- መጽሐፍ ቅዱስ አማኝ ወደሆነች ቤተክርስቲያን ሂድና፣ ከሁሉም በላይ ኢየሱስን ከሚያከብሩ ሌሎች ሰዎች ጋር በማምለክ አብረሃቸው ማደግ ጀምር (ፍሊጵስዩስ 3፡7)